Seattle Office of Economic Development

# Back to Business (ወደ ንግድ መመለስ) ፕሮግራም ማመልከቻ መመሪያ

ማመልከቻውን በአንድ ጊዜ ሞልቶ ለመጨረስ ዝግጁ ይሁኑ። የጀመሩትን መረጃ ማስቀመጥ (save) እና በኋላ ተመልሰው መጨረስ አይችሉም። **ማመልከቻዎች እስከ ታህሳስ 2026 ድረስ ወይም ገንዘቦች እስኪያልቁ ድረስ ክፍት ናቸው።**

*ይህ መመሪያ ማመልከቻዎን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለማዘጋጀት እንዲረዳዎ ነው።* **ማመልከቻውን በኢንተርኔት ላይ በእንግሊዝኛ መሙላት አለብዎት።** ጥያቄዎችን ለመመለስ እና ማመልከቻዎን እንዲያጠናቅቁ ለመርዳት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሰራተኞች አሉን። የጽሑፍ ትርጉም ወይም የቃል አስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ በ(206)684-8090 መደወል ይችላሉ። እባክዎ የእርስዎን ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ተመራጭ ቋንቋ እና የተፈለገውን የድጋፍ ዓይነት የያዘ የድምጽ መልዕክት ይተዉ።

ለተጨማሪ ጥያቄዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ማመቻቻዎች ወይም የተደራሽነት መረጃ፣ እባክዎን የኢኮኖሚ ልማት ቢሮን (Office of Economic Development) በ206-684-8090 ወይም በOED@seattle.gov ያግኙ።

*ለሲያትል ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚገቡ የማመልከቻ ተዛማጅ መረጃዎች የሕዝብ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ። የሕዝብ አባላት መደበኛ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ ሊጠይቁ ይችላሉ። በዋሽንግተን ስቴት ለሕዝብ ይፋ ማድረጊያ ህግ (PDA፡RCW 42.17) ምክንያት መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ሊደረጉ ይችላሉ። የሕጉን ቅጂ ለመጠየቅ፣ በኦሊምፒያ የሚገኘውን የዋሽንግተን ኮድ ከላሾች ቢሮ (Code Revisers' Office) በ (360) 786 6777 ደውለው ይገናኙ።*

## የንግድ ብቁነት

ብቁ ለመሆን፣ ንግድዎ አነስተኛ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡-

- አሁን ላይ የሚሰራ/ቀኑ ያላለፈበት የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆን።
- ሁሉንም የፌዴራል፣ የስቴት እና የከተማ ህጎች እና ደንቦችን ማክበር።
- በአሁኑ ጊዜ ለአገልግሎት ክፍት እና የሚንቀሳቀስ ወይም ደግሞ የተፈረመ የኪራይ ውል በማስረጃነት ማቅረብ የሚችል ለአገልግሎት ክፍት ለመሆን እያቀደ ያለ ንግድ ነው።
- በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ መገኘት።
- ከአምስት (5) የማይበልጡ ቦታዎች ያለው።
- በገለልተኛ ባለቤት የተያዘና የሰንሰለት ንግድ ያልሆነ።
    - **በገለልተኛ ባለቤትነት የተያዙ** ፍራንቻይዝ ንግዶችም ለማመልከት ብቁ ናቸው።
- ለትርፍ የተቋቋመ ንግድ ወይም ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም፣ 501(c)(3)፣ 501(c)(6)፣ ወይም 501(c)(9) መሆን።
- ከ50 የማይበልጡ የሙሉ ጊዜ አቻ ሠራተኞች መኖር።
- ለሲያትል ከተማ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች መምሪያ (City of Seattle Department of Finance and Administrative Services) በንግድ እና ሥራ (Business and Occupation) ግብሮች ላይ ሪፖርት በተደረገው መሠረት የንግዱ ዓመታዊ የተጣራ ገቢ ከ$1,000 ዶላር በላይ የሚሠራ እና ከ$7 ሚሊዮን ዶላር የማይበልጥ መሆን አለበት።
- በአንድ **ህዝቡን በሚያገለግል** አካላዊ ቦታ እና/ወይም በተንቀሳቃሽ የጭነት መኪናዎች ላይ ሆኖ የሚሰራ መሆን አለበት።

## የካሳ መስፈርቶች

ወደ ንግድ ሥራ መመለስ ፕሮግራም የሚሠራው በማካካሻ ሞዴል ነው፣ ይህም ማለት የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ለማግኘት አመልካቾች አስቀድመው መሣሪያዎችን ገዝተዋል ወይም ለጥገና ክፍያ ከፍለዋል ማለት ነው። ለግዢ እና/ወይም ለተጠናቀቁ ጥገናዎች የተከፈለበትን ክፍያ መጠየቂያ ወይም ደረሰኝ (ኞች) ማቅረብ አለብዎት። **ግምቶች እና/ወይም የዋጋ ጥቅሶች ተቀባይነት አይኖራቸውም።**

የገንዘብ እርዳታ ስጦታው መጠን ለሚከተሉት ወጪዎች ተመላሽ ለማድረግ የሚፈልጉት ትክክለኛ መጠን ይሆናል፡-

- **የሱቅ የፊት ለፊት ጥገና ፈንድ፡-** ከፍተኛው የካሳ መጠን $5,000 ነው።
- **የሱቅ ፊት ለፊት ደህንነት ፈንድ፡-** ከፍተኛው የካሳ መጠን 10,000 ዶላር ነው።

Seattle Office of Economic Development

## ማመልከቻው ለሚከተሉት እንዲያመለክቱ ይፈቅድልዎታል፡-

### የሱቅ ፊት ለፊት ጥገና ፈንድ፡-

የሱቅ ፊት ለፊት ጥገና ፈንድ፡- በጁላይ 1 ቀን 2024 ወይም ከዛ በኋላ ለደረሰ ጉዳት ወይም ሌላ የንብረት ውድመት የሱቅ የፊት ለፊት ጥገና ክፍያ ካሳ ይሰጣል። የሚመለሰው ገንዘብ ለአንድ ክስተት እስከ 5,000 ዶላር የሚደርስ ወጪን ይሸፍናል። **በአንድ የካላንደር ዓመት ውስጥ ለእያንዳንዱ ጣሪያው $5000 ለሆነ ክስተት እስከ 3 የገንዘብ እርዳታ ስጦታዎች** መቀበል ይችላሉ።

ለእያንዳንዱ ብቁ ክስተት፣ ከማመልከትዎ በፊት የሚከተለውን መረጃ ማዘጋጀት አለብዎት፡-

- ለተጠናቀቁ ጥገናዎች የክፍያ ማረጋገጫ (የደረሰኝ(ኞች) ቅጂ እና/ወይም የክፍያ መጠየቂያ)።
- የሲያትል ፖሊስ መምሪያ ክስተት ቁጥር። *ከሌልዎት፣ እባክዎ የክስተት ቁጥር ለመቀበል የኢንተርኔት ላይ የኋላ ሪፖርት ያስገቡ፡-* Online Crime Reporting - Police | seattle.gov *(የኢንተርኔት ላይ ወንጀል ሪፖርት ማድረግ - ፖሊስ | seattle.gov)*።

ብቁ የሆነ የሱቅ ፊት ለፊት ንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት የሚከተሉትን ያጠቃልላል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፡-

- በሮች
- መቆለፊያዎች
- አጥሮች
- የግቢ በሮች
- ምልክቶች
- የተሰበሩ ወይም የተጫሩ መስኮቶች

### የሱቅ የፊት ለፊት ደህንነት ፈንድ

የሱቅ የፊት ለፊት ደህንነት ፈንድ ጥፋትን እና የንብረት ውድመትን ለሚከላከለው የደህንነት ማሻሻያ የአንድ ጊዜ ክፍያን ይሰጣል። **በአንድ ንግድ እስከ $10,000 የአንድ ጊዜ ክፍያ** ሊደርስዎት ይችላል። ለሱቅ ፊት ለፊት የደህንነት ፈንድ ለማመልከት የጥፋት ወይም የውድመት ማስረጃ **አያስፈልግም**።

ብቁ ለመሆን፣ ከማመልከትዎ በፊት የሚከተለውን መረጃ ማዘጋጀት አለብዎት፡-

- የተጠናቀቀ የወንጀል መከላከል በአካባቢ ዲዛይን (Crime Prevention Through Environmental Design (CPTED)) የደህንነት ግምገማ። ይህ ከሲያትል ፖሊስ ዲፓርትመንት የወንጀል መከላከያ አስተባባሪ ጋር በመሆን ሊጠናቀቅ ይችላል።
- ለደህንነት ማሻሻያዎች የክፍያ ማረጋገጫ፣ እንደ ደረሰኝ(ዎች) እና/ወይም የክፍያ መጠየቂያ ቅጂ።

Seattle Office of Economic Development

## የCPTED የደህንነት ግምገማ ምንድነው?

ለንግዶች የCPTED የደህንነት ግምገማዎች ወንጀልን በአካባቢ ዲዛይን (CPTED) መከላከል እና ሌሎች የተረጋገጡ የወንጀል መከላከል ስልቶችን መሰረት ያደረጉ ናቸው። የደህንነት ጉዳዮችን ለመወያየት እና ደህንነትን ለማሻሻል እና የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ የሚረዱ ዕቅዶችን እና ሀብቶችን ለመለየት ዕድል ይሰጣል። የCPTED የደህንነት ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ የተገዙ የደህንነት እርምጃዎች ገንዘቡን ለማስመለስ ብቁ ናቸው።

የCPTED የደህንነት ግምገማ ቀጠሮ ለመያዝ፣ እባክዎን በእርስዎ ክልል ውስጥ ለሚገኘው የወንጀል መከላከያ አስተባባሪ (Crime Prevention Coordinator) ኢሜል ያድርጉ።

- የእርስዎን ቀጠና እዚህ ያግኙ።
- የአካባቢዎን የወንጀል መከላከያ አስተባባሪ እዚህ ያግኙ።
- በኢሜልዎ ውስጥ፣ እባክዎ የሚከተለውን መረጃ ማካተትዎን ያረጋግጡ።
    - የንግድዎ ስም
    - የንግድዎ አድራሻ
    - ለሱቅ የፊት ለፊት ደህንነት ፈንድ የCPTED ደህንነት ግምገማ እየጠየቁ መሆኑን ይጻፉ።

## ብቁ ወጪዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን በነዚህ ብቻ አይወሰኑም፡-

- መብራት
- የደህንነት መስኮት ማጠናከሪያ ፕላስቲክ
- የመስኮት መትከያዎች
- “ሲሰበር የማይበታተን” የታሸገ መስታወት ያለው መስኮት
- የንግድ ቦታ እና መንገድ መሪ ምልክቶች (ክፍት ነው፣ ዝግ ነው፣ መግቢያ፣ መውጫ፣ የሥራ ሰዓቶች)።
- አድራሻ መሰየሚያ
- የመግቢያ ቦታዎች አካባቢ እንደ ጽጌረዳዎች ወይም ሆሊ ቁጥቋጦዎች ያሉ የመከላከያ አታክልት
- የተፈቀዱ የመንገድ መትከያዎች ( የመንገድ ላይ የቤት ዕቃዎች መመሪያዎችን ይመልከቱ)
- መቀስ በር
- የመስኮት ታጣፊ የደህንነት መዝጊያ
- የበር መቆለፊያ
- የመስኮት መቆለፊያዎች
- የማንቂያ/ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶች (መሣሪያዎቹን ብቻ፣ መቆጣጠሪያ አገልግሎቶቹን እና የደኅንነት ካሜራዎቹን ሳያካትት)
- ጊዜያዊ የመስኮት ወይም በር ማሸጊያ እንጨት
- የመስኮት ጥገና ወይም መተካት ወጪ
  የበር ጥገና ወይም መተካት ወጪ
  የግቢ በር ጥገና ወይም መተካት

## ወደ ንግድ መመለስ ፕሮግራሙ ለማመልከት ብቁ ያልሆኑ ወጪዎች

እነዚህ ገንዘቦች የደህንነት ካሜራዎችን መግዛት፣ ለደህንነት ሰራተኞች የሚከፈል ክፍያ ወይም የተሰረቁ ዕቃዎችን መተካት አይሸፍኑም።

https://www.seattle.gov/neighborhoods/historic-preservation/historic-districtstel:%20+1%20(206)%20684-0228እነዚህ ገንዘቦች ሕገወጥ የግድግዳ ላይ መጻፍን አይሸፍኑም። ሕገወጥ የግድግዳ ጽሑፎችን ማስወገድ ካስፈለገ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ:-

- https://www.seattle.gov/Documents/Departments/SPU/EnvironmentConservation/GraffitiWaiverForm.pdfhttps://www.seattle.gov/Documents/Departments/SPU/EnvironmentConservation/GraffitiWaiverForm.pdfሕገወጥ ግራፊቲ (የግድግዳ ጽሑፎችን) በኦንላይን ቅጹ በኩል ሪፖርት ያድርጉ።
- Find It/Fix It (አግኝ/ጠግን) መተግበሪያን ይጠቀሙ።
- ወደ ከተማው የግራፊቲ ሪፖርት መስመር በ (206) 684-4243 ይደውሉ።

ስለ ከተማዋ የግራፊቲ መከላከል እና ማስወገድ ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ በዚህ ገጽ ላይ ይገኛል።

ንግድዎ በታሪካዊ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ፣ ከCPTED ጋር የተያያዘ ኢንቨስትመንት ከመግዛትዎ በፊት የፈቃድ ሰርተፍኬት (Certificate of Approval) ማግኘት ሊኖርብዎ ይችላል። ንግድዎ ታሪካዊ ወረዳ ውስጥ መሆኑን እዚህ ያረጋግጡ።

በታሪካዊ ዲስትሪክት ውስጥ ስላሉ የንግድ ሥራዎች መስፈርቶች ጥያቄ ካልዎት የሲያትል የሰፈሮች ታሪካዊ ጥበቃ መምሪያ (Seattle Department of Neighborhoods Historic Preservation) ቡድን ጋር በ (206) 684-0228 ይደውሉ።

## በኦንላይን የማመልከት ሂደት

ማመልከቻው አንዴ ከገባ በኋላ በበርካታ የግምገማ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል። የማመልከቻዎን ሁኔታ ለማሳወቅ ከእያንዳንዱ የግምገማ ደረጃ በኋላ አውቶማቲክ ኢሜሎች ይላክሉዎታል። የጎደለ ወይም ያልተሟላ መረጃ ካለ ኢሜል ይደርስዎታል።

ማመልከቻዎ ሲደርስ ማረጋገጫ ኢሜል ይደርስዎታል። መስፈርቶቹን ካላሟሉ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ ምላሽ ካልሰጡ የማሰናበት ኢሜል በማንኛውም ጊዜ ሊላክ ይችላል።

## ወደ ንግድ መመለስ ፕሮግራም መገኛ አድራሻ መረጃ

ለተጨማሪ ጥያቄዎች፣ ለጽሑፍ ትርጉም ወይም ለቃል አስተርጓሚ፣ ለአካል ጉዳተኞች ማመቻቻዎች ወይም የተደራሽነት መረጃ እና የቴክኒክ ድጋፍ እባክዎን ለOED_BackToBusiness@seattle.gov ኢሜይል ያድርጉ።

Seattle Office of Economic Development

# የማመልከት ሂደት ጥያቄዎች

እባክዎ የማመልከቻውን ክፍል 1 ከመጀመርዎ በፊት ከዚህ በታች ያሉትን የማመልከቻ ጥያቄዎች ይመልከቱ።

*ይህ መመሪያ ማመልከቻዎን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለማዘጋጀት እንዲረዳዎ ነው። ማመልከቻውን በኢንተርኔት ላይ በእንግሊዝኛ መሙላት አለብዎት። ጥያቄዎችን ለመመለስ እና ማመልከቻዎን እንዲያጠናቅቁ ለመርዳት ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሰራተኞች አሉን።* **የጽሑፍ ትርጉም ወይም የቃል አስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ በ(206)684-8090 መደወል ይችላሉ።** እባክዎ የእርስዎን ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ተመራጭ ቋንቋ እና የተፈለገውን የድጋፍ ዓይነት የያዘ የድምጽ መልዕክት ይተዉ።

*ለሲያትል ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚገቡ የማመልከቻ ተዛማጅ መረጃዎች የሕዝብ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ። የሕዝብ አባላት መደበኛ ጥያቄ በማቅረብ መረጃ ሊጠይቁ ይችላሉ። በዋሽንግተን ስቴት ለሕዝብ ይፋ ማድረጊያ ህግ (PDA፡RCW 42.17) ምክንያት መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ ሊደረጉ ይችላሉ። የሕጉን ቅጂ ለመጠየቅ፣ በኦሊምፒያ የሚገኘውን የዋሽንግተን ኮድ ከላሾች ቢሮ (Code Revisers' Office) በ (360) 786 6777 ደውለው ይገናኙ።*

---

## ክፍል 1፡- የመገኛ አድራሻ መረጃ

*እባክዎን ከዚህ በታች የገባው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጡ። የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ማመልከቻዎን በተመለከተ አዲስ ነገር ሲኖር እርስዎን እና ንግድዎን ለማግኘት ይህንን መረጃ እንጠቀማለን።*

እርስዎ ባለቤቱ ነዎት?

- አዎ
- አይ

የባለቤቱ መጠሪያ ስም፡-

የባለቤቱ የአያት ስም፡-

ኢሜል፡-

ኢሜልዎን ያረጋግጡ፡-

ስልክ ቁጥር፡-

ስልክ ቁጥሩን ያረጋግጡ፡-

*የንግዱ ህጋዊ ስም። እባክዎን የንግድዎን ስም በሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃድዎ ላይ እንደሚታየው ያስገቡ፡-*

ቢዝነስ DBA (ንግድ ሥራው የሚሰራው እንደ)፡ *የተመዘገበው የንግድዎ ስም በመባልም ይታወቃል፣ ይህ አብዛኛውን ጊዜ በብዙዎች የሚታወቀው ስም ነው። አንዳንድ ንግዶች DBA ላይኖራቸው ይችላል፡-*

*የሱቅዎ አካላዊ አድራሻ። "የአሁን ቦታ" የሚለውን የሚጠቀሙት ማመልከቻውን በንግድ ቦታዎ ሆነው እያጠናቀቁ ከሆነ ብቻ ነው፡-*

- አድራሻ (*ለምሳሌ 1234 Main St.)*
- አድራሻ 2
- ከተማ
- ግዛት/ስቴት
- ዚፕ ኮድ

በኦገስት 2025 እንደገና ከተከፈተ ጀምሮ ለሱቅ የፊት ለፊት ጥገና ፈንድ ከዚህ ቀደም አመልክተዋል? ይህ ከመጀመሪያው ከሴፕቴምበር 2022 እስከ ጁላይ 2024 ፈንድ የደረሱ የገንዘብ ስጦታዎችን አያካትትም።

- አዎ
- አይ

አዎ ከሆነ፣ የበፊቱ ማመልከቻዎ የማመልከቻ ቁጥር ስንት ነው? (ግዴታ አይደለም)። *ይህ የመጨረሻው ማመልከቻዎ የማረጋገጫ ኢሜል ውስጥ ሊገኝ ይችላል።*

*ተጨማሪ የመገኛ አድራሻ መረጃ ማቅረብ ይፈልጋሉ? ይህን መረጃ እርስዎ ባስገቡት የገንዘብ ድጋፍ ሽልማት ማመልከቻ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎችን ለመላክ የምንጠቀመው ይሆናል።*

- አዎ
- አይ

መጠሪያ ስም፡-
የአያት ስም፡-
ኢሜል፡-
ኢሜልዎን ያረጋግጡ፡-
ስልክ ቁጥር፡-
ስልክ ቁጥሩን ያረጋግጡ፡-

# ክፍል 2፡- የብቁነት ምዘና

*ብቁነትዎን ለማረጋገጥ እባክዎ ከታች ያሉትን ጥያቄዎች ይመልሱ።*

1. **ንግድዎ የሚሠራ የሲያትል ከተማ የንግድ ፈቃድ አለው?** *ብቁ ለመሆን ንግድዎ የሚሠራ የሲያትል የንግድ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል። የሚሰራ ፍቃድ እንዳልዎ ለማየት የንግድ መፈለጊያ መሳሪያን ይጠቀሙ።*
    - አዎ
    - አይ

2. **የንግድ ሥራዎ በአሁኑ ጊዜ ለአገልግሎት ክፍት እና የሚንቀሳቀስ ወይም ደግሞ የተፈረመ የኪራይ ውል በማስረጃነት ማቅረብ የሚችል ለአገልግሎት ክፍት ለመሆን እያቀደ ያለ ንግድ ነው?**
    - አዎ
    - አይ

3. **ንግድዎ በሲያትል ከተማ ወሰኖች ውስጥ ይገኛል?** *ሲያትል ውስጥ ያሉ ንግዶች ብቻ ብቁ ናቸው።*
    - አዎ
    - አይ

4. **ንግድዎ ስንት ቦታዎች አሉት?** *ሶስት ወይም ከዚያ ያነሰ ቦታዎች ያላቸው ንግዶች ብቻ ብቁ ናቸው።*
    - 1
    - 2
    - 3
    - 4
    - 5
    - ከ 5 በላይ

5. **ንግድዎ ፍራንቻይዝ ነው?**
    - አዎ
    - አይ

6. **ንግድዎ ከ51 ያነሰ የሙሉ ጊዜ አቻ ሰራተኞች (FTEዎች) አሉት? ለማረጋገጥ ይህንን** *FTE ማስያ ይጠቀሙ። 50 FTEዎች ወይም ከዚያ ያነሰ ያላቸው ንግዶች ብቻ ብቁ ናቸው።*
    - አዎ
    - አይ

7. **ለሲያትል ከተማ የፋይናንስ እና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች መምሪያ በንግድ እና ሥራ (B&O) ግብሮች ላይ ሪፖርት በተደረገው መሠረት ንግዴ ከ$1,000 ዶላር በላይ እና ከ $7,000,000 ዶላር የማይበልጥ ዓመታዊ የተጣራ ገቢ አለው።** *ብቁ መሆን*

*የሚችሉት በዓመት ከ$1,000 እስከ $7 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ያላቸው ንግዶች ብቻ ናቸው።*

- አዎ
- አይ

8. **ንግድዎ የሚሠራው አካላዊ ቦታ ላይ ነው?** *ለዚህ የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ብቁ ለመሆን የምግብ መኪናዎችን ጨምሮ ብቁ ሱቆች ለህዝብ ዝግጁ ሆነው ክፍት መሆን አለባቸው።*
    - አዎ
    - አይ

9. **ንግድዎ ተንቀሳቃሽ የምግብ መኪና ነው?**
    - አዎ
    - አይ

10. **ንግድዎ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የኪራይ ወይም የኢንቨስትመንት ንብረት ነው?** *የአጭር ጊዜ ኪራዮች ኤርቢኤንቢን (Airbnb)፣ ቭርቦን(Vrbo)፣ ወዘተ ያካትታሉ።* ***ሱቆቻቸውን በሊዝ ወይም በኪራይ የያዙ የንግድ ባለቤቶች ማመልከቻ ለማስገባት ብቁ ናቸው።*** *የኪራይ ወይም የኢንቨስትመንት ንብረት ንግዶች ብቁ አይደሉም።*
    - አዎ
    - አይ

11. **ንግድዎ አንድ ታክሲ፣ ተሳፋሪ የሚጋሩት፣ ወይም የምግብ ማድረሻ አገልግሎት ነው (እንደ ኡበር፣ ሊፍት፣ ቢጫ ካብ፣ ዶር ዳሽ የመሳሰሉ)?** *የታክሲ፣ ተሳፋሪ የሚጋሩት እና የምግብ ማድረሻ አገልግሎቶች ብቁ አይደሉም።*
    - አዎ
    - አይ

12. **በሲያትል ማዘጋጃ ቤት የሕግ አንቀጽ 6.270 መሠረት ንግድዎ እንደ "የአዋቂ መዝናኛ" ንግዶች ቁጥጥር ይደረግበታል?** *ስለ እነዚህ ደንቦች [በሲያትል ማዘጋጃ ቤት ህግ 6.270](#) ላይ የበለጠ ማንበብ ይችላሉ። የአዋቂዎች መዝናኛ ንግዶች ብቁ አይደሉም።*
    - አዎ
    - አይ

# ክፍል 3፡- የፕሮግራም ምርጫ

**ፕሮግራም ይምረጡ፡-** *ከአንድ በላይ መምረጥ ይችላሉ።*

- **የሱቅ ፊት ለፊት ጥገና ፈንድ፡-** በጁላይ 1 ቀን 2024 ወይም ከዛ በኋላ ለደረሰ ጉዳት ወይም ሌላ የንብረት ውድመት የሱቅ የፊት ለፊት ጥገና ክፍያ ካሳ ይሰጣል። ብቁ የሆኑ ንግዶች በአንድ የካላንደር ዓመት ውስጥ ለእያንዳንዱ ጣሪያው $5000 ለሆነ ክስተት እስከ **ሶስት የገንዘብ እርዳታ ስጦታዎች ሊቀበሉ ይችላሉ።**
  - በዚህ ማመልከቻ ላይ ለምን ያህል የሱቅ የፊት ለፊት ጥገና የገንዘብ ስጦታዎች ማመልከት ይፈልጋሉ? ንግዶች ቢበዛ ሶስት የጥገና የገንዘብ እርዳታ ስጦታዎችን ሊያገኙ ይችላሉ።
    - አንድ
    - ሁለት
    - ሶስት

- **የሱቅ ፊት ለፊት ደህንነት ፈንድ፡-** ውድመትን እና የንብረት ጉዳትን ለመከላከል ለደህንነት ማሻሻያ ገንዘብ መልሶ ይሰጣል። ብቁ የሆኑ ንግዶች **በአንድ ንግድ እስከ $10,000 የአንድ ጊዜ ክፍያ።** *እንደ የሲያትል ፖሊስ መምሪያ የወንጀል መከላከያ አስተባባሪ ዓይነት ባለማረጋገጫ ባለሙያ ጋር የተሟላ የCPTED የደህንነት ግምገማ ማጠናቀቅ አለብዎት። የCPTED የደህንነት ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ ብቻ የተገዙ የደህንነት እርምጃዎች ገንዘቡን ለማስመለስ ብቁ ናቸው።*
  - **የ CPTED የደህንነት ግምገማ አጠናቅቀዋል?**
    - አዎ
    - አይ

Seattle Office of Economic Development

# የሱቅ የፊት ለፊት ጥገና የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ጥያቄዎች

## ክስተት 1

*የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ለማመልከት ለሚፈልጉት ለእያንዳንዱ ክስተት የተለየ የጥያቄዎች ስብስብ አለ። ለእስከ ሶስት ክስተቶች የእርዳታ ገንዘብ ማመልከት ይችላሉ። እባክዎ ለእያንዳንዱ ክስተት ለአንድ የጥያቄዎች ስብስብ ብቻ ምላሽ ይስጡ።*

**1. ክስተቱ የደረሰበት የንግዱ አካላዊ አድራሻ ምንድነው?**

- አድራሻ (*ለምሳሌ 1234 Main St.*)
- አድራሻ 2
- ከተማ
- ግዛት/ስቴት
- ዚፕ ኮድ

**2. የገንዘብ ድጋፍ እየጠየቁ ያለው ክስተት የተከሰተበት ቀን ምንድነው?**

**3. እባክዎ የሲያትል ፖሊስ መምሪያ የክስተት ሪፖርትዎን ቁጥር (ዎች) እዚህ ያስገቡ።** *ከሌልዎት የክስተቱን ቁጥር ማግኘት እና የመስመር ላይ የኋላ ሪፖርት ማቅረብ ይችላሉ፡-* [Online Crime Reporting - Police | seattle.gov (*የኢንተርኔት ላይ ወንጀል ሪፖርት - ፖሊስ |* Seattle.gov)]**፡-**

**4. በእርስዎ የሱቅ ፊት ላይ የደረሰውን ጉዳት በተሻለ የሚገልጸው ምንድን ነው?**

- የተሰበረ መስኮት
- የተሰበረ በር
- የተሰበረ መቆለፊያ
- የተሰበረ አጥር
- የተሰበረ የግቢ በር
- የተሰበረ ምልክት
- ሌላ:- _______

**5. እባክዎ ያጋጠሙ ሌሎች ጉዳቶችን ይግለጹ፡-**

**6. (አማራጭ) እባክዎ የጉዳቱን ፎቶ(ዎች) ይስቀሉ ካልዎት።**

## ደጋፊ ሰነዶች እና መረጃዎች

*እባክዎ የገንዘብ ድጋፍ ከሚጠይቁበት ክስተት ቀን ጋር የሚዛመዱ ደጋፊ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ብቻ ያስገቡ። ለሚያመለክቱበት ለእያንዳንዱ ክስተት አዲስ የጥያቄዎች ስብስብ ይመጣል።*

1. **ማስመለስ የሚፈልጉት ጠቅላላ ወጪ ስንት ነው?**
https://www.seattle.gov/police/need-help/property-crimes/online-reporting
2. **ከሚከተሉት ብቁ ዕቃዎች/ጥገናዎች ለንግድዎ የገዙት የትኛውን ነው? (የሚመለከተዎን ሁሉ ይምረጡ)**

- በሮች
- መቆለፊያዎች
- አጥሮች
- የግቢ በሮች
- ምልክቶች
- ጊዜያዊ የመስኮት ወይም በር ማሸጊያ እንጨት
- የመስኮት ጥገና ወይም መተካት ወጪ
- የበር ጥገና ወይም መተካት ወጪ
- የግቢ በር ጥገና ወይም መተካት
- የውጭ መብራት መጠገን ወይም መተካት
- ሌላ:- ______________________

3. **እባክዎ የገዙትን ሌሎች ዕቃዎች/ ያደርጓቸውን ጥገናዎች ይዘርዝሩ።** *በብቁ ዕቃዎች ዝርዝሩ ውስጥ ያልተካተቱ ዕቃዎች እንደየሁኔታው የሚታዩ ይሆናል።*

4. *እባክዎ ተመላሽ እንዲደረግልዎ የሚፈልጉትን ለጥገናው የከፈሉትን ጠቅላላ ወጪ የሚያሳዩ ደረሰኝ(ዎች) እና/ወይም <u>የተከፈለ</u> ኢንቮይስ(ዎች) ወይም ከተዛማጅ የባንክ ወይም የክሬዲት ካርድ መግለጫ ጋር የተያያዘ ኢንቮይስ(ዎች) ቅጂ ይስቀሉ። የዋጋ ግምቶችን መቀበል አንችልም።* (.JPG፣ .PDF፣ .DOCX እና XLSXን ጨምሮ አብዛኛዎቹን የፋይል ዓይነቶች መስቀል ይችላሉ። እባክዎ ቪዲዮዎችን አይጫኑ)።

5. **በሱቅ ፊት ለፊት ያለው ንብረት ጉዳት በንግድዎ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድሯል? (የሚመለከተዎን ሁሉ ይምረጡ)**
   a. የገንዘብ ኪሳራ
   b. የስራ መቋረጥ (ማለትም የስራ ሰዓታት መቀነስ፣ የንግድ አሠራሮችን መቀየር)
   c. የሸቀጦች መበላሸት ወይም መጥፋት
   d. በሰራተኞች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ (ማለትም ሞራል ወይም መልቀቅ)
   e. የደንበኛ ትራፊክ መቀነስ
   f. የደህንነት ወጪዎች መጨመር
   g. የኢንሹራንስ ተከፋይ መጨመር
   h. አይመለከትም

i. ሌላ፡- ____________________

**6. አደጋው ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ የንግድዎ የኢንሹራንስ መጠን ጨምሯል?**

a. አዎ
   i. አዎ ከሆነ በስንት ፐርሰንት? ______
- አይ
- አይመለከትም

**7. የንግድ ኢንሹራንስዎ ውድመትን ይሸፍናል?**

a. አዎ
b. አይ

Seattle Office of Economic Development

# የሱቅ የፊት ለፊት ደህንነት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ጥያቄዎች

1. **የCPTED የደህንነት ግምገማ አጠናቅቀዋል?**
    - አዎ
    - አይ

2. **እባክዎ ስለ CPTED ደህንነት ግምገማዎ የሚከተለውን መረጃ ያቅርቡ፦**
    - የCPTED ደህንነት ግምገማ ቀን፦
    - የ CPTED ግምገማ የተጠናቀቀበት የንግድ አድራሻ፦
        - አድራሻ (*ለምሳሌ 1234 Main St.*)
        - አድራሻ 2
        - ከተማ
        - ግዛት/ስቴት
        - ዚፕ ኮድ

    - የCPTED ግምገማውን ያካሄደው ማነው?
        - ባርብ ቢዮንዶ (Barb Biondo)፣ ምዕራብ ክልል (West Precinct)
        - ጆ ኤለንባስ (Joe Elenbaas)፣ ምስራቅ ክልል (East Precinct)
        - ጄኒፈር ሳተርዋይት (Jennifer Satterwhite) ፣ ደቡብ ምዕራብ ክልል (Southwest Precinct)
        - ማርክ ሰለሞን (Mark Solomon)፣ ደቡብ ክልል (South Precinct)
        - ማቲው ብራውን (Matthew Brown)፣ደቡብ ምዕራብ ክልል (SW Precinct)
        - ኬትሊን ዬፕ (Katelyn Yep)፣ ሰሜን ክልል (North Precinct)
        - አና ካርፔንተር (Ana Carpenter)፣ ሰሜን ክልል (North Precinct)
        - ሌላ፦ ________________

3. **ከሚከተሉት ብቁ ዕቃዎች/የመከላከያ የደህንነት እርምጃዎች ውስጥ የገዙት እና/ወይም ለንግድዎ የተተገበሩት የትኞቹ ነው? (የሚመለከተው ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ)**

    - የአላርም ሲስተሞች
    - መቀስ በሮች
    - ወደላይ የሚከፈቱ በሮች
    - በመስኮቶች ላይ የሚደረግ የደህንነት ፕላስቲክ
    - የደህንነት መብራት
    - መቆለፊያዎች
    - ሲሰበር የማይበታተን መስታወት
    - ሌላ፦ ________________

Seattle Office of Economic Development

## ደጋፊ ሰነዶች እና መረጃዎች

**1. ማስመለስ የሚፈልጉት ጠቅላላ ወጪ ስንት ነው?**

2. **እባክዎ ተመላሽ እንዲደረግልዎ የሚፈልጉትን ለደህንነት ማሻሻያ የከፈሉትን ጠቅላላ ወጪ የሚያሳዩ ደረሰኝ(ዎች) እና/ወይም የተከፈለ ኢንቮይስ(ዎች) ወይም ከተዛማጅ የባንክ ወይም የክሬዲት ካርድ መግለጫ ጋር የተያያዘ ኢንቮይስ(ዎች) ቅጂ ይስቀሉ። የዋጋ ግምቶችን መቀበል አንችልም።** (.JPG፣ .PDF፣ .DOCX እና XLSXን ጨምሮ አብዛኛዎቹን የፋይል ዓይነቶች መስቀል ይችላሉ። እባክዎ ቪዲዮዎችን አይጫኑ)

**3. እባክዎ የደህንነት እርምጃዎችን መተከላቸውን የሚያሳይ ፎቶ(ዎች) ካልዎት ይጫኑ። (አማራጭ)**

Seattle Office of Economic Development

# ክፍል 4:- የንግድ መረጃ

1. *እባክዎን ስለ ዋናዎቹ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች እና ንግድ ተጨማሪ መረጃ ያስገቡ።*

2. **የሚመርጡት ቋንቋ ምንድን ነው?** *እባክዎን ከታች ካለው ተቆልቋይ ማውጫ ይምረጡ።*
    - እንግሊዝኛ
    - ስፓኒሽ
    - ካንቶኒዝ
    - ታይዋንኛ
    - ታይሻንኛ
    - ማንዳሪን
    - ቬትናምኛ
    - የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ
    - አማርኛ
    - አረብኛ
    - የቡታን ቋንቋ
    - በርምኛ/ ካረን
    - ኮንጉሊዝ
    - ፋርሲ
    - ጃፓንኛ
    - ኮሪያኛ
    - የላኦስ ቋንቋ
    - ክመር/ካምቦዲያንኛ
    - ኦሮምኛ
    - ኔፓሊኛ
    - ፓሽቶ/ ዳሪ
    - ራሺያንኛ
    - ሶማሊኛ
    - ተጋሎግ
    - ታይ
    - ትግርኛ
    - የዩክሬን ቋንቋ
    - ሌላ:- _______

3. **ዘርዎ/ጎሳዎ ምንድነው?** *ከዚህ በታች ካሉት ዋና ዋና ምድቦች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ የበለጠ ይምረጡ።*

- እስያዊ
- ጥቁር ወይም አፍሪካ አሜሪካዊ
- ሂስፓኒክ ወይም ላቲኖ/ና/ንክስ
- መካከለኛ ምስራቃዊ ወይንም ሰሜን አፍሪካዊ
- ነባር ተወላጅ አሜሪካዊ ወይም የአላስካ ተወላጅ
- የሃዋዩ ተወላጅ ወይም የፓስፊክ ደሴት ተወላጅ
- ነጭ
- ሌላ
- አለመናገር እመርጣለሁ።

4. **ጾታዎን እንዴት ይገልፁታል?** *እባክዎን ከዝርዝሩ ውስጥ ይምረጡ።*
    - ወንድ
    - ሴት
    - ሁለትዮሽ ያልሆነ
    - አለመግለጽ እመርጣለሁ
    - ሌላ

5. **ንግዱ ስንት ባለቤቶች አሉት?**

6. **ተጨማሪ የንግድ ባለቤቶች ስሞች።** *እባክዎን ከዚህ በታች ተጨማሪ የንግድ ባለቤቶችን ይዘርዝሩ፦*

**7. እባክዎ ከንግድዎ አይነት ጋር በይበልጥ የሚስማማውን ምድብ ይምረጡ፡-**

- የችርቻሮ ንግድ፡- ሱቅ
- የምግብ አገልግሎቶች፡- ምግብ ቤቶች እና ካፌዎች
- የምግብ አገልግሎቶች፡- ባሮች ወይም መጠጥ ቤቶች
- የምግብ አገልግሎቶች፡- ተንቀሳቃሽ፣ የምግብ አቅርቦት እና የምግብ ገበያዎች
- የግል አገልግሎቶች (ውበት፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ የሕጻናት እንክብካቤ፣ ደረቅ ጽዳት፣ የግል ወይም የሸማች አገልግሎቶች፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ/መዝናኛ የቤት ውስጥ እንቅስቃሴ ቦታዎች፣ በውሊንግ መጨወቻዎች፣ ጂሞች፣ የጨዋታ መገልገያዎች፣ ወዘተ.)
- የጤና እንክብካቤ (የሕክምና ቢሮዎች፣ ክሊኒኮች፣ የአዛውንቶች ማስታመሚያ ቤቶች፣ የመታሸት አስታማሚዎች/ ቴራፒስቶች፣ የጥርስ ሐኪሞች)
- የንግድ አገልግሎቶች (ሕጋዊ፣ የሂሳብ ሥራ፣ ግብይት፣ ለንግዶች ማማከር)
- ሙያዊ ወይም ቴክኒካዊ አገልግሎቶች (የስነ ሕንፃ ድርጅቶች፣ የምህንድስና ኩባንያዎች)
- የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች (ፊልም፣ የምሽት ህይወት፣ ልዩ ዝግጅቶች፣ ፎቶግራፊ፣ ማስታወቂያ፣ ግራፊክ ዲዛይን፣ ይዘት መፍጠር፣ ፋሽን፣ አልባሳት እና ጨርቃ ጨርቅ፣ ስነ ጽሑፍ፣ ህትመት፣ ጋዜጠኝነት፣ የቅጅ አርትዖት፣ የኪነጥበብ እና የባህል ተቋማት እና የምሽት ህይወት ቦታዎች)
- አስተዳደራዊ አገልግሎቶች (የአስተዳደር ድጋፍ አገልግሎቶች)
- ግብርና ወይም የተፈጥሮ ሀብቶች (የደን ልማት፣ እርሻ ማረስ፣ ማዕድን፣ ዓሳ ማጥመድ)
- የሕፃናት እንክብካቤ ወይም መዋዕለ ሕጻናት
- የግንባታ ወይም ከባድ የጣቢያ ሥራ (ሥራ ተቋራጮች፣ ከባድ ሲቪል፣ መኖሪያ)
- የትምህርት አገልግሎቶች (ስልጠና፣ የርቀት ትምህርት)
- ፋይናንስ፣ ኢንሹራንስ ወይም የርስት/ ቤቶች ሀብት (ባንኮች፣ የመዋዕለ ንዋይ ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ደላሎች፣ የርስት/ የቤት ሀብቶች ደላሎች)
- መስተንግዶ (ሆቴሎች)
- የሕይወት ሳይንስ ወይም የስነ ሕይወት ተክኖሎጂ (biotech) (ምርምር እና ልማት፣ የመድኃኒት አምራቾች፣ የህክምና መሣሪያዎች)
- ማምረት፡- የምግብ እና የመጠጥ ምርት (የምግብ አምራቾች፣ የባህር ምግብ ማቀነባበሪያዎች፣ ቢራ ፋብሪካዎች፣ የወይን ጠጅ አምራቾች፣ የአረቄ ማምረቻዎች)
- ማምረት፡- ሌላ
- የጽሑፍ ማተሚያ ወይም ሌላ መረጃ (ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጽሐፍ ማተም፣ የተንቀሳቃሽ ፊልም ፕሮዳክሽን)
- ማህበራዊ አገልግሎቶች (የተቋማት የምግብ አገልግሎቶች፣ መኖሪያ ቤት፣ የድንገተኛ ጊዜ አገልግሎቶች፣ የማህበራዊ ሥራ)
- ሶፍትዌር፣ በክላውድ ላይ የተመሰረቱ (cloud-based) ምርቶች እና አገልግሎቶች፣ ወይም የቴሌኮምዩኒኬሽን (ሶፍትዌር፣ የክላውድ ክምፕዩቲንግ፣ የኢንተርኔት አቅራቢዎች፣ የቴሌኮም አቅራቢዎች)
- መጓጓዣ ወይም የመጋዘን ሥራ (የጭነት መጓጓዣ፣ የባቡር ሐዲድ፣ የጭነት ማስተላለፍ፣ አየር መንገዶች፣ ማከማቻዎች፣ የመሬት ማጓጓዣ፣ መልእክት አመላላሾች)
- መጓጓዣ፡- በውሃ ላይ (የመዝናኛ መርከቦች፣ በውሃ ላይ የተመሠረቱ ጉብኝቶች፣ ጭነት)
- የቆሻሻ አገልግሎቶች (ቆሻሻ አያያዝ)
- የጅምላ ሻጮች፣ የጅምላ ነጋዴዎች

Seattle Office of Economic Development

8. **የተዋሃደ የንግድ መለያ (UBI) ቁጥር።** *የኩባንያዎ የተዋሃደ የንግድ መለያ (UBI) ኩባንያዎን ከስቴት ወኪል ድርጅቶች ጋር የሚመዘገብበት እና በዋሽንግተን ውስጥ ንግድ እንዲሰሩ የሚያስችልዎ ባለ ዘጠኝ አሃዝ ቁጥር ነው። የእርስዎን UBI [በገቢዎች መምሪያ (Department of Revenue) ድህረ ገጽ]() ላይ ያግኙ።*

9. **የሲያትል የንግድ ፈቃድ የታክስ ምስክር ወረቀት ቁጥር።** *ለዚህ የገንዘብ እርዳታ ስጦታ ብቁ ለመሆን ትክክለኛ የሲያትል የንግድ ሥራ ፈቃድ ያስፈልጋል። የፈቃድ ቁጥሮች ከ4 እስከ 6 አሃዞች አሏቸው። የፍቃድ ቁጥርዎን ለማግኘት ወደ የሲያትል [ፈቃድ እና የታክስ አስተዳደር ድህረ ገጽ]() ይሂዱ።*

10. **የንግዱ የመላላኪያ አድራሻ (ከላይ ካለው ቦታ የተለየ ከሆነ)።** ለገንዘብ እርዳታ ስጦታው ቼክ የምንልክበት አድራሻ ይህ ነው። *የመላላኪያ አድራሻዎ እንደ ዋናው የንግድ አድራሻዎ ተመሳሳይ ከሆነ እነዚህን ቦታዎች ባዶ ይተውዋቸው።*
    - አድራሻ (*ለምሳሌ 1234 Main St.*)
    - አድራሻ 2
    - ከተማ
    - ግዛት/ስቴት
    - ዚፕ ኮድ

11. **ስለዚህ የገንዘብ እርዳታ ስጦታ እንዴት ሰሙ?**
    - የOED ድህረ ገጽ
    - የOED ብሎግ
    - ማህበራዊ ሚዲያ
    - የአነስተኛ ንግድ ምክር ቤት
    - የንግድ ሥራ ማሻሻያ ማህበር (Business Improvement Association)
    - የንግድ ድርጅት
    - በወሬ ወሬ
    - ሌላ

Seattle Office of
Economic Development

## ክፍል 5፡- የዕውቅና ማረጋገጫ እና ማመልከቻ ማስገባት

በዋሽንግተን ስቴት ሕጎች መሠረት በሐሰት ምስክርነት እንደምጠየቅ በመረዳት ከዚህ ቀደም ብሎ የተሰጠው ቃል እውነት እና ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ ወይም አውጃለሁ። የተሰጠው መረጃ ሁሉ ከሚመለከታቸው የስቴት ወይም የፌዴራል መንግስት ወኪል ድርጅቶች ሁሉ ጋር ሊረጋገጥ ይችላል። ይህ የሲያትል ንግድ እና ሥራ (B&O) የግብር አቅራቦት መረጃን ለመገምገም እና ለማረጋገጥ ፈቃድ መስጠትን ያካትታል። ይህንን የእርዳታ ማመልከቻ ሲፈርሙ እና ሲያስገቡ፣ በንግድዎ የቀረበውን የግብር መረጃ የኢኮኖሚ ልማት ጽ/ ቤት እንዲያገኝ እና እንዲገመግመው ፈቃድ እየሰጡ ነው።

ማመልከቻዎን ለማስገባት ይህንን መግለጫ ማረጋገጥ ወይም ማወጅ አለብዎት።

በዚህ ማመልከቻ ውስጥ የገባው መረጃ ሁሉ እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

*ማመልከቻ አስገባ*